## የጊዜው ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡

## የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቀሙትን ፡ ሀብቶች ፡ የሚያስለቅቅበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

ሃሪሰን ፡ ሲ ፡ ዳኒንግ ፡*

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአዋጅ ፡ ተቋቋመ ።[1] ምንም ፡ እንኳን ፡ የአውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ መሥራትና ፡ መጠበቅ ፡ ሥልጣን ፡ ከሥራና ፡ ማመላለሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተዛወረበት ፡ ምክንያት ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ግልጽ ፡ ባይሆንም ፡ የሥልጣን ፡ ማዛወሩ ፡ የተደረገው ፡ የአስተዳደር ፡ ቅልጥፍናን ፡ ለማግኘት ፡ ይመስላል ።[2] እንዲያውም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ እቅዶች ፡ ከውጭ ፡ ከተገኙት ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታዎች ፡ አብዛኛውን ፡ የሰጠው ፡ ለማደሻና ፡ ለልማት ፡ የቆመው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ባንክ ፡ በ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የመጀመሪያውን ፡ የ፳ ፡ ሚሊዮን ፡ የአሜሪካን ፡ ብር ፡ ብድር ፡ እንዲሰጥ ፡ ይህን ፡ የአስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ለውጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ፡ አድርጐ ፡ የገመተው ፡ ይመስላል ።[3] የተቋቋመበት ፡ ምክንያቶች ፡ ግልጽ ፡ ባይሆኑም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሥራዎችን ፡ ከሚያከናውኑትና ፡ ጠቃሚ ፡ ከሆ

* በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ረዳት ፡ ዲንና ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰር ። በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለሚደረገው ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ለጸሐፊው ፡ መግለጫ ፡ በመስጠት ፡ የሚከተሉት ፡ ሰዎች ፡ ስለአደረጉት ፡ እርዳታ ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ፡- አቶ ፡ ሽፈራው ፡ ብዙነህ ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ምክትል ፡ ዋና ፡ መሃንዲስ ፤ አቶ ፡ ዘውዱ ፡ መሸሻ ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሕግ ፡ መኰንን ፤ አቶ ፡ ከበደ ፡ በየነ ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የመተላለፊያ ፡ መብት ፡ መኰንን ፤ አቶ ፡ ሰይፉ ፡ የተሻወርቅ ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ምክትል ፡ የመተላለፊያ ፡ መኰንን ፤ ሻለቃ ፡ ለማ ፡ ገብረጻድቅ ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ከመተላለፊያ ፡ መብት ፡ ቅርንጫፍ ፡ ሚስተር ፡ ፓርክ ፡ ዊልሰን ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የቀድሞ ፡ የገንዘብና ፡ ያስተዳደር ፡ ሥራ አስኪያጅ ፤ ሚስተር ፡ ሮበርት ፡ ስኰት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሕግ ፡ ጠበቃ ።

1. የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ .ም . አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፲፮ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፴ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፮ ። ይህ ፡ አዋጅ ፡ የጸደቀው ፡ ጥር ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሆን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ ከዚሁ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።
2. ሐምሌ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጁን ፡ ከአረቀቁት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ከሆኑት ፡ ከሚስተር ፡ ሮበርት ፡ ስኰት ፡ ጋራ ፡ የተደረገ ፡ ኢንተርቪው ። ለመጀመሪያ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ የባለሥልጣኑ ሥራ ፡ አስኪያጆችና ፡ ሠራተኞች ፡ የተገኙት ፡ ከአሜሪካን ፡ ቢሮ ፡ ኦቭ ፡ ፓብሊክ ፡ ሮድስ ፡ ነው ። ይህም ፡ ድርጅት ፡ ምናልባት ፡ ለመሥራት ፡ የፈለገው ፡ ከአንድ ፡ ራሱን ፡ ከቻለ ፡ ድርጅት ፡ ጋር ፡ ነው ።
3. ይህ ፡ ለውጥ ፡ ተፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ የሚታወቀው ፡ ከአዋጁ ፡ መግቢያ ፡ ነው ፡-
“የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንን ፡ የማመላለሻ ፡ ጐዳናዎችና ፡ ሥራ ፡ ለማሻሻል ፡ ምኞታችን ፡ ስለሆነ ፤ ይህንንም ፡ ምኞታችንን ፡ ለመፈጸም ፡ ለማደሻና ፡ ለልማት ፡ ከቆመ ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ባንክ ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ ስላደረግን ፡ ኅብረቱንም ፡ ለማግኘት ፤ የአውራ ፡ ጐዳናዎችን ፡ ማስፋፊያና ፡ መጠበቂያ ፡ ፕሮግራም ፡ አድሚኒስትራሲዮን ፡ ማሻሻል ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ” ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፲፮ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፴ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፮ ። ራሱን ፡ የቻለ ፡ ባለሥልጣን ፡ ማቋቋም ፡ በገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮች ፡ የበለጠ ፡ ታማኝነትና ፡ የተሻለ ፡ አስተዳደር ፡ የሚያስገኝ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ታስቦ ፡ ነው ።

ኑት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ድርጅቶች ፡ አንዱ ፡ መሆኑን ፡ አሳይቷል ።[4]

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎችን ፡ ለመሥራትና ፡ ለመጠገን ፡ ስለሆነ ፡[5] ባለሥልጣኑ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መሬቶች ፡ ለመውሰድ ፡ የሚያስችል ፡ ሥልጣን ፡ መሰጠቱ ፡ ተገቢ ፡ ነው ።[6] የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፫(መ) ፡ እንደሚለው ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ “ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ አድርጐ ፡ የግል ፡ መሬቶችን ፡ ለመውሰድና ፡ በመሬቶች ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ ቤቶች ፡ አዝመራዎች ፡ አታክልቶችና ፡ ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የሚገባውን ፡ ግምት ፡ ለመወሰን ፡”[7] ይችላል ።

---

4. በተቋቋመ ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ሰፋ ፡ ካለው ፡ የአውራ ፡ ጐዳናዎችን ፡ የመጠገንና ፡ የማሻሻል ፡ ሥራ ፡ ሌላ ፡ ከ፳ሺ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ የሚበልጡ ፡ በበጋም ፡ ሆነ ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ የሚያገለግሉትን ፡ መንገዶች ፡ በመሥራትና ፡ በማደስ ፡ ረድቷል ። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ኢትዮፒያ ፦ ፕሮግሬስ ፡ ኢን ፡ ሃይ ፡ ዌይ ፡ ትራንስፖርት ፡ (፲፱፻፷፯ ኢ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፡ ገጽ ፡ ፪ ። ከ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ሥራና ፡ ማደሻ ፡ የአሜሪካን ፡ ፶፰ሚሊዮን ፡ ወጪ ፡ ሲደረግ ፡ ከዚህም ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ፹፪ ፡ እጅ ፡ የተገኘው ፡ ከውጭ ፡ ብድሮችና ፡ እርዳታዎች ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ በገጽ ፡ ፬ ፡ ይመለከቷል ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥም ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ጥበቃ ፡ የአሜሪካን ፡ ፵፯ ፡ ሚሊዮን ፡ ያህል ፡ ወጪ ፡ ሆኗል ። ከዚያው ።
5. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የአውራ ፡ ጐዳናን ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውነው ፡ በተለዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ “የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ የአውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ ማሻሻልና ፡ መጠበቅ ፡” ተግባር ፡ ቢሰጥም ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ በግልጽ ፡ ታውቀው ፡ የተዛወሩት ፡ ተግባሮች ፡ “ከዚህ ፡ በፊት ፡ በሥራና ፡ ማመላለሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሠራ ፡ የነበረው ፡ ሥራ ፡ ተግባርና ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡” ናቸው ። አንቀጽ ፡ ፫ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፲፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፩ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የሥራና ፡ ማመላለሻ ፡ ሚኒስትር ፡ “የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንን ፡ መንገዶች ፡ ድልድዮችን ፡ ለመሥራትና ፡ እየተጠባበቀም ፡ ለማደስ ፡ አላፊ ፡” ቢሆን ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ የሚወስን ፡ ትእዛዝ ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፩ (ለ) ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ቁጥጥር ፡ ስር ፡ ያሉት ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ “መንገዶችን ፡ አደባባዮችን ፤ ድልድዮችን ፤ መንሸርሸሪያዎችንና ፡ የአትክልት ፡ ቦታዎችን ፡ መክፈት ፡ ማስቀረት ፤ መጠበቅ ፤” የመሳሰሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ ለመወሰን ፡ እንዲችሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቷቸዋል ፤ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ (፫) ፡ (ሀ) ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፤ ቁጥር ፡ ፸፬ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፯ ። በተጨማሪም ፡ የጐዳናዎችና ፡ መንገዶች ፡ አከፋፈል ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቊጥር ፡ ፷፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፲ ፡ (ተቀጣይ) ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ይመለከቷል ። በተግባር ፡ ላይ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ ከአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋራ ፡ የተለየ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ መንገድ ፡ የመሥራትና ፡ የመጠበቅ ፡ ተግባራቸውን ፡ ራሳቸው ፡ ሲያከናውኑ ፡ ቆይተዋል ።
6. የዚሁ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፲ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ “በዚህ ፡ አዋጅ ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ (መ) እንደተመለከተው ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ አድርጐ ፡ በግል ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ለመግባት ፡ ወይም ፡ መሬቶችን ፡ ለመውሰድ ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ መታየት ፡ ወይም ፡ መፈቀድ ፡ የለበትም ። በመሬቶቹ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኙት ፡ ቤቶች ፤ አዝመራዎች ፡ አታክልቶች ፤ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ባለሥልጣኑ ፡ የወሰነው ፡ ግምት ፡ በሚገባ ፡ መሆኑንና ፡ አለመሆኑን ፤ ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ባለጥቅሞች ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የግምት ፡ አከፋፈል ፡ ይመርመርልኝ ፡ ሲል ፡ በተወሰደው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ መሬቱ ፡ ባለበት ፡ አውራጃ ፡ በሚገኘው ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል” ። ምንም ፡ እንኳን ፡ አዋጁ ፡ ያሜሪካኖችን ፡ አባባል ፡ ተከትሎ ፡ “የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ አድርጐ ፡ — መሬቶችን ፡” መውሰድ ፡ (ኤሚነንት ፡ ዶሜይን ፡) ቢልም ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አባባል ፡ “ንብረትን ፡ ማስለቀቅ ፡” በሚለው ፡ ሐረግ ፡ እንጠቀማለን ።
7. አንቀጽ ፡ ፫ ፡ (መ) ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፲፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፫ ። በተጨማሪም ፡ የ፲፱፻፵፫ን ፡ ዓ ፡ ም ፡ መምሪያ ፡ ቊጥር ፡ ፴፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ ይመለከቷል ።

ስለዚህም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፫ (መ) ፡ የሚገባው ፡ ግምት ፡ ከሚወሰንላቸው ፡ ነገሮች ፡ ጥንትም ፡ ሆነ ፡ አሁን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ግምት ፡ የሚታየው ፡ የንብረት ፡ ዓይነት ፡ የሆነውን ፡ መሬትን ከዝርዝሩ ፡ ትቶታል ።[8] ይህም ፡ በግድፈት ፡ ወይም ፡ በስህተት ፡ የተደረገ ፡ አይደለም ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንም ፡ ከ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የግል ፡ የሆኑ መሬቶችን ፡ የሚወስደው ፡ ምንም ፡ ግምት ፡ ሳይሰጥ ፡ ነው።[9] ለዚህም ፡ የተሰጠው ፡ ምክንያት ፤ አውራ ፡ ጐዳናው ፡ ሲሠራ ፡ በአካባቢው ፡ ያለውን ፡ የመሬት ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ይህ ፡ የዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ አውራ ፡ ጐዳናው ፡ ካመጣቸው ፡ ሌሎች ፡ ጥቅሞች ፡ ጋራ ፡ ሲደመር ፡ ለመንገዱ ፡ ሥራ ፡ ሲባል ፡ መሬታቸው ፡ በከፊል ፡ ለተወሰደባቸው ፡ ባለ ፡ ንብረቶች ፡ በቂ ፡ ግምት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነው ።[10] ይህ ፡ አስተያየት ፡ ቢኖርም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ በተወሰደው ፡ መሬት፡ ላይ ፡ ለሚገኙት ፡ ቤትን ፡ ለመሳሰሉት ፡ ንብረቶች ፡ በአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፫ (መ) ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሚገባውን ፡ ግምት ፡ ሰጥቷል ።[11]

---

8. አንቀጽ ፡ ፳፫ (መ) ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ከመሬቱ ፡ ላይ ፡ ለተወሰዱት ፡ ንብረቶች ፡ ነው ፡ ስለሚል ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ወይም ፡ አሸዋ ፡ ላሉት ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ለሚገኙት ፡ ንብረቶች ፡ ግምት ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚከለክል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተገምቷል ። እንዲህ ፡ ዓይነቱን ፡ ለመሥሪያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ንብረቶች ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በብዛት ፡ ሲወስድ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ የሚከፍለው ፡ ላስከተለው ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ ድንጋይ ፡ በሚፈለጥበት ፡ ቦታ ፡ አጠገብ ፡ ለጠፋው ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ግምት ፡ ይከፈላል ። ይህም ፡ ተግባር ፡ ክስ ፡ እንዲበዛ ፡ ሲያደርግ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንን ፡ የማይደግፉ ፡ ፍርዶችም ፡ አሉባቸው። ለምሳሌ ፡ ያሀል ፡ ጣፋ ፡ ሰኚ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ (ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፪፻፺፩/፺፪ ፡ ዓ ፡ ም) (ያልታተመ)። በከፊል ፡ ሲነበብ ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ከውኃ ፡ በታች ፡ ያለውም ፡ ጭምር ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቱ ፡ ነው ፡" በሚለው ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ ምክንያት ፡ የነዚህ ፡ የድንጋይ ፡ ፈለጣ ፡ ጉዳዮች ፡ አወሳሰን ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኗል ። ከመሬት ፡ በታች ፡ የሚገኙት ፡ ድንጋይና ፡ ሌላም ፡ ለመሥሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ንብረቶች ፡ ለግል ፡ ንብረትነት ፡ የተፈቀዱ ፡ ናቸው ፡ ከተባሉ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ "የመለቀቃቸው ፡" ጥያቄ ፡ የሚነሳው ።

9. ከአቶ ፡ ከበደ ፡ በየነ ፤ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የመተላለፊያ ፡ መኰንን ፡ ጋራ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተደረገ ፡ ኢንተርቪው ። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ፡ ፳፫ (መ) ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሬት ፡ እንዲወስድና ፡ ላንዳንድ ፡ ለተጠቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የኪሣራ፡ግምት፡እንዲሰጥ ፡ ስለሆነ ፡ አንዳንድ ፡ የባለሥልጣኑ ፡ ባልደረቦች ፡ እንደሚሉት ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ለሌሎች ፡ ንብረቶች ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዳይከፍል ፡ ስለታገደ ፡ በዚህ ፡ አስተሳሰብ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ አከፋፈሉን ፡ ሊለውጥ ፡ ቢፈልግም ፡ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡በከፊል ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሥራ ፡ ሠፈር ፡ እንዲሆን ፡ ሲወሰድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ወይም ፡ የሚስተካከለው ፡ መሬት ፡ ከመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ ለተወሰደበት ፡ ባለንብረት ፡ ተሰጥቶአል ። ለተወሰደበት ፡ መሬት ፡ ምትክ ፡ የተሰጠው ፡ አዲስ ፡ መሬት ፡ በዋጋ የሚመጣጠነው ፡ ከሆነ ፡ ባለመሬቱ ፡ እንዲለቅ ፡ ለተገደደበት ፡ መሬት ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ተከፍሎታል ፡ ማለት ፡ ነው ።

10. ከአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ባልደረቦች ፡ ጋራ ፡ በተደረጉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኢንተርቪዎች ፡ የተገኙ ። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ በተዘጋጀበት ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊው ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ ታስቦ ፡ ወይም ፡ ተገልጾ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ የሚያስደፍር ፡ ማስረጃ ፡ አላገኘም ።

11. የሚታመኑ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ለማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ቢሆንም ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ብዙ ፡ አልነበረም ። ለመጀመሪያዎቹ ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ተግባር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትን ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ ወደ ፡ ጥቅም ፡ መመለስ ፡ ስለነበረ ፡ ብዙ ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ችግር ፡ አልገጠመውም ። እንዲያውም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የመተላለፊያ ፡ ቅርንጫፍ ፡ የተቋቋመው ፡ በ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ይመስላል ። መልካም ፡ ምሳሌዎች ፡ የሚሆኑ ፡ በቅርቡ ፡ የተከፈሉ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የተገለጹት ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡- የኢትዮጵያ ፡ $፱ሺ፪፻፳ ከ፺ ፡ ሣንቲም ፡ ለ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እና ፡ የኢትዮጵያ ፡ $፩ሺ፯፻፴፰ ፡ ለ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ። ለነዚህ ፡ ዓመቶች ፡ ዓመታዊውን ፡ ሪፖርት ፡ በቅደም ፡ ተከተልነታቸው ፡ በገጽ ፡ ፷፬ ፡ እና ፡ በገጽ ፡ ፷ ፡ ይመለከቷል ፡ ምናልባትም ፡ በተጨማሪ ፡ በመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ መሬትም ፡ በከፊል ፡ እንደ ፡ ኪሣራ ፡ ግምት ፡ ሳይሰጥ ፡ አልቀረም ።

## የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ እና ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ መንግሥት ፡

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ የወጣው ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ከተደረገ ፡ ለተወሰደው ፡ ንብረት ፡ በግልጽ ፡ ግምት ፡ መሰጠት ፡ አለበት ፡ በማይለው ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ነው ።[12] ነገር፡ ግን ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ንብረት ፡ ትክክለኛው ፡ ግምት ፡ እንዲሰጠው ፡ በግልጽ ፡ ያዛል ። የዚህም ፡ ሕገ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ እንደሚለው ፡ "በዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫፤ ወይም ፡ ፫ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ንብረቶች ፡ መወሰድ ፡ (ኤክስፕሮፕሪዬሽን) ፡ በተለይ ፡ በሚወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖና ፤ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተስማምቶበት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣው ፡ በሚኒስትር ፡ ትእዛዝ ፡ " ካልሆነ ፡"---በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ አይወሰድበትም ።" በተጨማሪም፡ "በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ አስቀድሞ ፡ ካልተከፈለ ፡ በቀር ፡ በግምቱም ፡ ስምምነት ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ በዳኝነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡" ንብረቱ ፡ አይወሰድም ።[13]

---

12. የዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ የሚለው ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ በሕግ ፡ እንደተጻፈው ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ከሚያስፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ በቀር ፡ በእጃቸው ፡ የያዙትን ፡ ገንዘባቸውንና ፡ ውለታቸውን ፡ ማንም ፡ ሊወስድባቸው ፡ አይችልም ፡" ነው ። ለእንግሊዘኛ ፡ አንባብያን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ፖልና ፡ ክላፐም ፡ ኢትዮፕያን ፡ ክንስቲቱሽናል ፡ ዲቬሎፕመንት ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ በገጾች ፡ ፫፻፳፯ — ፫፻፴ ፡ እና ፡ በኢትዮፒያን ፡ ኦብዘርቨር ፡ (፲፱፻፷፪ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ቮልዩም ፰ ፡ በገጾች ፡ ፫፻፷፫ ፡ ፫፻፷፯ ፡ በሙሉ ፡ ታትሞ ፡ ይገኛል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ታትሞ ፡ ያልወጣ ፡ ስለ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተጻፈ ፡ አንድ ፡ ማብራሪያ ፡ ኀተታ ፡ በመንግሥት ፡ መወረስ ፡ ስለ ፡ ማይገባቸው ፡ መሬቶች ፡ ሲያወሳ ፡ የሚከተለውን ፡ አስተያየት ፡ ሰጥቷል ፡ መንግሥት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለሕዝብ ፡ ደህንነት ፡ የሚጠቅሙ ፡ እንደ ፡ ምሽጐች ፡ ጐዳኖች ፡ ገበያዎች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፤ ትምህርት ፡ ቤቶች ፤ ሆስፒታሎች ፤ ከተማዎች ፡ ወይም ፡ ሌሎችም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ ለመሥራት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ካገኘው ፡ በሕጉ ፡ እንደተወሰነው ፡ የምክር ፡ ቤቶቹ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከወሰኑ ፡ ባለመሬቱ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ ተመጣጣኝ፡ ግምት ፡ ይሰጠዋል ፡ ባለንብረቱ ፡ ከፈቀደም ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ ይሰጠዋል ፡" (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ። ክፍል ፡ ፫፪ ፤ ደምሴ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትና ፡ ምክር ፡ ቤት ፤ ታሪካዊ ፡ መዝገብ ። [ያዘጋጁው ፡ ማስታወሻ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተዘጋጀው ፡ ባማርኛ ፡ ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተሰጠው ፡ በኤስ ፡ ራይት ፡ አማካኝነት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ከተተረጐመውና ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ በፖልና ፡ ክላፐም ፡ መጽሐፍ ፡ በገጾች ፡ ፫፻፴፩ ፤ ፴፻፴፬ ፡ ከሚገኘው ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ በመተርጐም ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነው ፡ የመጀመሪያው ፡ ጽሑፍ ፡ ባለመገኘቱ ፡ መሆኑን ፡ እንገልጻለን ።]

13. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ። አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ በተጨማሪ ፡ የተባለው ፡ የሚኒስትር ፡ ትእዛዝ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተስማምቶበት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ መውጣት ፡ አለበት ፡ ይላል። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንዱ ፡ ችሎት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ "ስለ ፡ ግል ፡ ንብረቶች ፡ መወሰድ ፡ (ኤክስፕሮፕሪዬሺን ፡) በተለይ ፡ በሚወጣው ፡ ሕግ ፡ " የሚለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ንብረትን ፡ ስለ ማስለቀቅ ፡ የተደነገጉትን ፡ ደንቦች ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ተገቢ ፡ አስተያየት ፡ ሰጥቷል ፡ ሳክፌት ፡ ሶቼታ ፡ አኖኒማ ፡ ከሳሽ ፤ የማዕድንና ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ሚኒስቴር ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤ የኢት ፡ ሕገ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፯) ፡ ገጾች ፡ ፶፮-፶፱ ። የፍትሐ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ንብረት ፡ መወሰድ ፡ በተለይ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ስላልነበረ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ፡የሆነ ፡ መሬት ፡ የማስለቀቅ ፡ ተግባር ፡ ሊከናወን ፡ አይችልም ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ሰጥቷል ። ሐጂ ፡ አሊ ፡ አሕመድ ፡ አቦኝ ፡ ከሳሽ ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ተሠሳሽ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ፳፻፴፪/፶) (ያልታተመ) ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ እና ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ለተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ በተሰጠው ፡ አተረጓጐም ፡ ላይ ፡ በተመሠረተው ፡ የባለሥልጣኑ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተግባር ፡ መካከል ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መቃረን ፡ ቢኖርም ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ የባለሥልጣኑ ፡ መሥሪያ ቤት ፡ ተግባር ፡ አልተለወጠም ። እንዲያውም ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ ተቃውሞ ፡ የገጠመው አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ ንብረታቸው ፡ የተወሰደባቸው ፡ ባለንብረቶች ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ወደ ፡ አካባቢያቸው ፡ በመምጣቱ ፡ ስለሚደሰቱ ፡ እና ፡ ለተወሰዱባቸው ፡ ቤቶች ፡ አዝመራዎችና ፡ "ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡" የተሰጣቸው ፡ ግምት ፡ አጥጋቢ ፡ ሆኖ ፡ ስለአገኙት ፡ ይመስላል ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ባለንብረት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ስለ ፡ ግምት ፡ አከፋፈል፡ የሚመለከቱትን ፡ አንቀጾች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ሲቃወም ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ አዋጁም ፡ ሆነ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ "የጠቅላላውን ፡ ጥቅም ፡" እንዲጠብቁ ፡ የታሰቡ ፡ ስለሆኑ ፡ ስለ ፡ ግምት አከፋፈል ፡ የሚመለከቱ ፡ የአዋጁ ፡ አንቀጾች ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አይቃረኑም ፡ ብሎ ፡ ወሰነ ።[14] ይህም ፡ ውጤት ፡ የተገኘው ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የግል ፡ ንብረትን ፡ የማስለቀቅ ሥልጣን ፡ የሚሰጡትን ፡ የአዋጁን ፡ አንቀጾች ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚያስችለውን ፡ የተሻሻለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይመለከት ፡ ነው ። "የበላይ ፡ ሕግን ፡" የሚገልጸው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ ከምትሆንባቸው ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ ከዓለም ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ሆኖ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ። ወደ ፡ ፊትም ፡ የሚሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፍርዶች ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ።" (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።) የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንም ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውንበት ፡ ሕግ ፡ የታወጀው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ ስለሆነ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እሱን ፡ የሚመለከት ፡ አይደለም ፡ ሊል ፡ ይችላል ።[15]

---

14. የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ እና ፡ እስካንስካ ፡ ኩባንያ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮ ፤ ኮሎኔል ፡ መብራቱ ፡ ፍስሐ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤ የኢ.ት ፡ ሕገ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፪ (ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፯) ፡ ገጾች ፡ ፴፫-፴፯ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ መፍለጥን ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆን ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በግል ፡ ንብረት ፡ ከተያዘ ፡ መሬት ፡ ድንጋይ ፡ እንዳይፈለጥ ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ፍርድም ፡ የግል ፡ ባለ ፡ ንብረቱ ፡ "ስለ ፡ ግምት ፡ መጠየቅ ፡ ነገር ፡ --- የሚያቀርቡት ፡ ክርክር ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ አያግድም" ቢልም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የወሰድነው ፡ የፍርድ ፡ አተረጓጐም ፡ ተገቢ ፡ ይመስላል ። ከዚያው ፡ በገጽ ፡ ፴፯።

15. ይህን ፡ አስተሳሰብ ፡ የ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የቴሌፎን ፡ አገልግሎት ፡ አዋጅን ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፲፬ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፱ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፲፩ ፡ በሚመለከተው ፡ በክቡር ፡ ልጅ ፡ አርአያ ፡ አበበ ፡ ከሳሽ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ መልስ ሰጭ ፡ ጉዳይ ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፯) ፡ የኢ.ት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ገጾች ፡ ፫፻ ፡ ፫፻፪ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ተጠቅሞበታል ። ስለ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ትርጉም ፡ ለመረዳት ፡ ፖልና ፡ ክላፕሃም ፡ ኢትዮፕያን ፡ ኮንስቲቱሽናል ፡ ዲቬሎፕመንት ፡ ቮልዩም ፡ ፩ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፡ ገጾች ፡ ፬፻፲፬-፬፻፲፯ ፤ እና ፡ ሚንስ ፡ "በመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተወሰኑ ፡ ጉዳዮችን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የማየት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተደገፈ ፡ ሥልጣን ፡ መነሻ ፡ ጥያቄዎች ፡" የኢ.ት ፡ ሕገ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፫ ፡ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጾች ፡ ፩፻፶፪ ፡ ፩፻፶፬ ፤ ይመለከቷል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ላስለቀቀው ፡ መሬት ፡ ግምት ባለመስጠቱ ፡ እርምጃው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ ለመቃረኑ ፡ እርግጠኛ ፡ ለመሆን ባይቻልም ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ በተጨማሪ ፡ ለመቃወም ፡ የሚቻለው ፡ ባለሥልጣኑ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለእርምጃው ፡ መሠረት ፡ አድርጐ ፡ የቆጠራቸውን ፡ የአዋጁን ፡ አንቀጾች ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለሚሽራቸው ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሕግ ፡ ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ፡ የተጻፉ ፡ የራሱ ፡ ድንጋጌዎች፡ አሉት ፤ እነዚህም ፡ ድንጋጌዎች ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚፈጽማቸውን ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ተግባር ፡ የሚመለከቱ ፡ ይመስላሉ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቊጥር ፡ ፩ሺ፬፻፷ — ፩ሺ፬፻፹፰ ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ግምት፡ አከፋፈልና ፡ "የአስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡" የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ሲያስለቅቁ ፡ ሊከተሉት ፡ የሚገባቸውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይደነግጋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ "የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡" የሚለው ፡ አነጋገር ፡ (ሕጉ ፡ መጀመሪያ ፡ በተጻፈበት ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ላድሚኒስትራሲዮን ፡ የሚል ፡ ነው ፡) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ባይተረጐምም ፡ ለማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸውን ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ያሉትን ፡ የሚያጠቃልል ነው ፡ ቢባል ፡ ተገቢ ፡ አተረጓጎም ፡ ይመስላል ።[16] መሬቱ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ አዝመራዎች ፡ ባይኖሩትም ፣ የአስተዳደር ፡ ክፍሉ ፡ ላስለቀቀው ፡ መሬት ፡ ተገቢውን ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ በገንዘብም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ መሬት እንዲከፍል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያስገድደዋል ። ስለዚህም ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፬(፩) እንዲህ ፡ ይላል ፡- "ስለ ፡ መሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ የሚከፈለው ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ መሰል ፡ ምትኩ ፡ መሬቱን ፡ ከማስለቀቁ ፡ የተነሣ ፡ በደረሰውና ፡ በተረጋገ

16. በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቂያ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እነማን ፡ መሆናቸው ፡ በሙሉ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። አንዱም ፡ አስተሳሰብ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በተፈጥሯቸው ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ ሲኖራቸው ፡ ሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ግን ፡ በግልጽ ፡ ሥልጣኑ ፡ ካልተሰጣቸው ፡ አይችሉም ፡ ይላል ። ሚኒስቴሮች ፡ ያልሆኑ ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ምሳሌዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡— የ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፣ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፳፮ ፣ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፣ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ (ሀ) ፤ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኤሌትሪክ ፡ መብራትና ፡ ኃይል ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ቻርተር ፣ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፲፫ ፣ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፣ ፲፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፫ ፣ አንቀጽ ፡ ፬ (ሠ) ፤ የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፣ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፣ ቊጥር ፡ ፩፻፴፩ ፣ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፣ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፣ ቊጥር ፡ ፫ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ (ሰ) ። የሆነ ፡ ሆኖ ፣ ለሚኒስቴሮችም ፡ ንብረት ፡ የማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠበት ጊዜ ፡ አለ ። ለምሳሌ ፣ የባሕር ፡ አዋጅ ፣ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፷፬ ፣ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፣ አንቀጽ ፡ ፵፯ ፣ ለአገር ፡ መከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፣ ለባሕር ፡ ክፍል ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ንብረቶች ፡ እንዲያስለቅቅ ፣ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ። ለባሕር ፡ መከላከያ ፡ ጉዳዮች ፡ ንብረትን ፡ የማስለቀቅ ፣ ሥልጣን ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ በሚወስን ፡ ትእዛዝ ፡ (ማሻሻያ ፡ ቊ. ፪) ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቊጥር ፡ ፵፯ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፤ ቊጥር ፡ ፳፫ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ መሠረት ፤ ቀጥተኛ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ መገናኛ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተዛውሮአል ። በተጨማሪ ፡ የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፖስታ ፡ አገልግሎት ፡ አዋጅ ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፵ ፣ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፣ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፣ ፳፪ ፣ አንቀጽ ፡ ፲፯ ፡ ይመለከቷል ። ይህም ፡ አንቀጽ ፡ "ራሱን ፡ የቻለ" ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የተባለውን ፡ የፖስታ ፡ ቤት ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ። ኮንሴስዮን ፣ የተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፣ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፣ ለመፈጸም ፡ ውል ፡ የገቡትም ፡ ጭምር ፣ በኮንሴሲዮኑ ፡ ስምምነት ፡ በግልጽ ፣ ሥልጣን ፣ ከተሰጣቸው ፡ ንብረትን ፡ ሊያስለቅቁ ፡ ይችላሉ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፩ሺ፬፻፷፪ ።

ጠው ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ይሆናል” (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ።[17] የታወቀ ፡ የመሬት ፡ ገበያ ፡ ካለ ፡ መሬቱ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ አዝመራዎች ፡ ቢኖሩትም ፡ ባይኖሩትም ፡ በገበያው ፡ ያለው ፡ የመሬቱ ፡ ዋጋ ፡ በባለንብረቱ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የተረጋገጠ ፡ ጉዳት ፡ ለመወሰኛ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የመሬት ፡ ገበያ ፡ ባይኖርም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈል ፡ የሚያስገድድበት ፡ ጉዳት ፡ ይደርሳል ።

መሬቱ ፡ ቢለማም ፡ ባይለማም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የኪሣራ፡ ግምት ፡እንዲከፈል ፡ ማስገደዱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሬት ፡ እንዲያስለቅቅ ፡ ሥልጣን ፡ ከሚሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ በቀር ፡ መሬት ፡ ማስለቀቅን ፡ የሚመለከቱት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ቊጥሮች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሻራቸውም ፡ ግልጽ ፡ ነው ።[18] በጣም ፡ ሰፊ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡[19] ስለተሻሩ ፡ ሕጐች ፡ የሚናገረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡- “ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለተተካ ፡ ተሽረዋል ።” ስለ ፡ መሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክቷል ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፰ (መ) ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፲ ፡ መሬት ፡ ስለማስለቀቅ ፡ የተደነገጉ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩ ፡ ደንቦች ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ የቀድሞ ፡ ደንቦች ፡ እንዳይሻሩ ፡ የሚያደርግ፡ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ ስለሌለ ፡ ደንቦቹ ፡ መሻራቸው ፡ የማይካድ ፡ ነው።

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ግን ፡ ይኸንን ፡ ውጤት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ አልተቀበለውም ።[20] የዚህም ፡ ምክንያት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ ከተ

---

17. ሕጉ ፡ መጀመሪያ ፡ በተጻፈበት ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ፩ሺ፬፻፸፬ ፡ (፩) የሚለው ፡ የኪሣራ ፡ ግምቱ ፡ *égale à la valeur du dommage actuel et certain* መሆን ፡ አለበት ፡ ነው ። በእንግሊዘኛው ፡ አክችዋል ፡ (*actual*) የሚለው ፡ ቃል ፡ “ያሁን ፡ የሆነ ፡” የማለት ፡ ስሜት ፡ እንጂ ፡ “በእርግጥ ፡ የደረሰ ፡” የሚለውን ፡ ስሜት ፡ የያዘ ፡ አይደለም ። የተርጓሚው ፡ ማስታወሻ ፡- የአማርኛው ፡ ቅጂ ፡ የፈረንሳይኛው ፡ ቅጂ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ ነው ።
18. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ሆነ ፡ ለሌላ ፡ በስም ፡ የተጠቀሰ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅት ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ አይሰጥም ። ስለዚህም ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና፡ባለሥልጣን፡ንብረት ፡ ለማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጠውን ፡ የተቋቋመበትን ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ እንዳልተሻረ ፡ አድርጐ ፡ መቁጠር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ አለዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ይህን ፡ የሚያስችለው ፡ ሥልጣን ፡ አይኖረውም ። ከላይ ፡ የሚገኘው ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፲፰ን ፡ ይመለከቷል ።
19. ጂ ፡ ክሽችኖቪች ፡ “ሕግና ፡ ባሕል ፡ (ልማድ ፡) በኢትዮጵያ ፡” የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ) ፤ ገጾች ፡ ፬፻፩ ፡ ፬፻፬-፬፻፭ ፤ ጂ ፡ ክሽኖቢች ፡ “ኤ ፡ ኒው ፡ ሌጂስለቲቭ ፡ አፕሮች ፡ ቱ ፡ ካስተመሪ ፡ ሎው ፡- ዘ ፡ ‘ሪፒልስ’ ፡ ፕሮቪዥን ፡ አቭ ፡ ዘ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲቪል ፡ ኮድ ፡ አቭ፡፲፱፻፷ ፡ ጆርናል ፡ አቭ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ስታዲስ ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቊጥር ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፡ገጽ ፡ ፶፯ ፡ ይመለከቷል ። በተጨማሪም ፡ የሚከተሉትን ፡ ይመለከቷል ፡- አር ፡ ሴድለር ፡ “ዘ ፡ ዲቬሎፕመንት ፡ አቭ ፡ ሊጋል ፡ ሲስተምስ ፡- ዘ ፡ ኢትዮፕያን ፡ ኤክስፒርየንስ ፡” ፡ አዮዋ ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮልዩም ፡ ፶፫ (፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፡ ገጾች ፡ ፭፻፷፪ ፡ ፭፻፺፬—፭፻፱ ጂ ፡ ቫንደርሊንደን ፡ “ስለ ፡ ‘የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ ፡’ የተሰጠ ፡ ተጨማሪ ፡ ማብራሪያ” ፤ የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፫ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ገጾች ፡ ፮፻፳፱ ፡ ፮፻፴ ፤ ጂ ፡ ክሽችኖቪች ፡ “ሕጉን ፡ ጥንታዊ ፡ ማድረግ ፡ አይሆንምን ? ሕግና ፡ ምንጮቹ ፡” የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፫ ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጾች ፡ ፮፻፱ ፡ ፮፻፲፪-፮፻፲፯ ፤ ጂ ፡ ቫንደርሊንደን ፡ “የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ ። ከ፲፫ኛው ፡ እስከ ፡ ፳ኛው ፡ መቶ ዓመት ፡” የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፫ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፡ ገጾች ፡ ፩፻፶፪ ፡ ፪፻፲፪—፪፻፲፭ ።
20. ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ሀብቶች ፡ ስለማስለቀቅ ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ መሻራቸውን ፡ ቢቀበሉም ፡ ይህ ፡ እምቢተኛነት ፡ አሁንም ፡ አለ ። በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰውንና ፡ አሁን ፡ በይግባኝ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ችሎት ፡ የቀረበውን ፡ ጣፋ ፡ ሰኚ ፡ ከሳሽ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ተከሳሽ ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቷል።

ከተለ ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቂያ ፡ ዋጋ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ስለሚል ፡ "ፍሬያማ" ፡ የአውራ ፡ ጐዳናን ፡ ሥራ ፡ ይቀንሳል ፡ የሚል ፡ ፍርሃት ፡ ይመስላል ። ይህም ፡ ፍርሃት ፡ አንዳንዱን ፡ የባለሥልጣኑን ፡ ሠራተኞች ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ እንዳይሆን ፡ እና ፡ ባለሥልጣኑ ፡ መሬት ፡ ባስለቀቀ ፡ ጊዜ ፡ ለመሬቱ ፡ ሳይሆን ፡ በመሬቱ ፡ ለሚገኙ ፡ ቤቶች ፡ አዝመራዎችና ፡ ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ብቻ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈል ፡ የሚያደርገው ፡ የቀድሞው ፡ ሕግ ፡ እንደገና ፡ እንዲወጣ ፡ እንዲከራከሩ ፡ አድርጓቸዋል ።[21]

ይህ ፡ ፍርሃት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ ተገቢ ፡ ቢመስልም ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ግምት ፡ አከፋፈል ፡ የተደነገጉትን ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ በጥንቃቄ ፡ መመርመር ፡ የአውራ ፡ ጐዳናዎችን ፡ ሥራና ፡ እድገት ፡ የመሰለ ፡ እቅድ ፡ በገንዘብ ፡ እጥረት ፡ ያሰናክላል ፡ የሚለውን ፡ ፍርሃት ፡ ለማስወገድ ፡ ሳያስችል ፡ አይቀርም ። በእርግጥ ፡ ዋናው ፡ ችግር ፡ የኪሳራ ፡ ግምት ፡ አወሳሰን ፡ ዘዴ ፡ ነው ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ ለተወሰደ ፡ "ንብረት ፡" "በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡" ፡ እንዲሰጥ ፡ ያዛል ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ከንብረቶች ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ ስለሆነ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ "ንብረት ፡" ሲል ፡ መሬትን ፡ አይጠቀልልም ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ አያዋጣም ።[22] ይህም ፡ አባባል ፡ የለማውንም ፡ ሆነ ፡ ያልለማውን ፡ መሬት ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። መሬት ፡ "ንብረት" ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ቢሆንም ፡ መሬት ፡ እንዲለቀቅ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈለው ፡ "በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት" ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ አያስረዳም ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመንግሥትና ፡ በግል ፡ ባለንብረት ፡ ጥቅሞች ፡ መካከል ፡ ትክክለኛ ፡ ሚዛናዊ ፡ ሁኔታን ፡ በመፍጠር ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከሚለው ፡ ጋራ ፡ የሚስማሙ ፡ በመሆናቸው ፡[23] በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የኪሳራ ፡ ግምት ፡

---

21 . የድሮው ፡ ደንብ ፡ እንደገና ፡ ቢደነገግ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ለመጠቀቀም ፡ ስለማይችል ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ መከራከሪያው ፡ በይበልጥ ፡ የተዳከመ ፡ እንደሚሆንበት ፡ መገንዘብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚወጣ ፡ ማንኛውም ፡ ሕግ ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ መስማማት ፡ ይኖርበታል ። ይህም ፡ ማለት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ በሚጠይቀው ፡ መሠረት ፡ ለሕዝብ ፡ ተፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የሚወሰድ ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈልበት ፡ ያስፈልጋል ። ስለ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ከላይ ፡ ገጽ ፪፻፲፩ ይመለከቷል ።

22 . የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እና ፡ የኢትዮጵያም ፡ ልማድ ፡ በጠቅላላው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የከተማ ፡ ቦታዎችም ፡ ሆኑ ፡ የባላገር ፡ የርሻ ፡ መሬቶች ፡ በቤተ ፡ ሰብም ፡ ሆነ ፡ በያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ባለመብትነት ፡ ሥር ፡ ቢገኙም ፡ የግል ፡ ንብረቶች ፡ መሆናቸውን ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳሉ ። ስለ ፡ ሌሎች ፡ የመሬት ፡ ዓይነቶች ፡ ትንሽ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ጉዳይ ፡ አለ ። ለምሳሌም ፡ "የግጦሽ ፡ መሬት" በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴ ፡ (መ) እንደተጠቀሰው ።

23 . አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ መብቶች ፡ የሚጠበቁት ፡ "በሕግ ፡ መሠረት" ነው ። "ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ " በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ "በሕግ ፡ መሠረት" የሚለው ፡ አለመኖሩን ፡ መገንዘብ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍ ፡ ፵፬ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ የሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ ካልተሟሉ ፡ በቀር ፡ የማንኛውም ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ እንዳይወሰድ ፡ ይከለክላል ። እነሱም ፡ በመጀመሪያ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ "ተስማምቶበት" ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣው ፡ በሚኒስትር ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ ሲኖርበት ፡ የስምምነቱ ፡ ዓይነት ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ አልተገለጸም ። በተጨማሪ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈልና ፡ በግምቱም ፡ ስምምነት ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ በዳኝነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መወሰን ፡ ይኖርበታል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ግምት ፡ የሚወሰንበትን ፡ አኳኋን ፡ የሚገልጸው ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ቢሆን ፡ የሰው ፡ ንብረት ፡ ሲወሰድ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ የመስጠት ፡ አስፈላጊነት ፡ የመነጨው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የአንድ ፡ ሕግን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ያለውን ፡ እንደገና ፡ የማየት ፡ ሥልጣን ፡ ቢጠቀምበት ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ግምት ፡ የወጣ ፡ ሕግን ፡ "ትክክለኛ ፡ ግምት" ሊያሰጥ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ለመሰረዝ ፡ ይችላል ።

ሲወሰን ፡ መደረግ ፡ ያለባቸውን ፡ ነገሮች ፡ በጥንቃቄ ፡ ማረጋገጥ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ነው ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተባለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ በመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ በደረሰው ፡ "[የ] ተረጋገጠው ፡ ጉዳት ፡" ልክ ፡ የሆነ ፡ ግምት ፡ መክፈል ፡ ነው ።[24] መሬት ፡ እንዲለቀቅ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ፡ መብት ፡ የነበራቸው ፡ ሰዎች ፡ መብታቸው ፡ ሲቀር ፡ ስለሚጐዱ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ለደረሰባቸው ፡ ጉዳት ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ መክፈል ፡ አለባቸው ፡ ብለን ፡ መጀመር ፡ አለብን ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንዳንድ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተነሳ ፡ የዚህ ፡ መሠረተ — አሳብ ፡ ጠቅላላ ፡ አግባብነት ፡ ይቀንሳል ፡— ከነዚህም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዋናው ፡ በቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፬ ፡ (፪) ፡ የሚገኘው ፡ "የአገማመት ፡ የሽምግልና ፡ ኮሚሲዮን ፡" የኪሣራ ፡ ግምት ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ በተሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ ምክንያት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ባልተደረገው ፡ የመሬት ፡ ክፍል ፡ የተገኘውን ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ በግምቱ ፡ ውስጥ ፡ ማስገባት ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ ነው ።[25] የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ በግምቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባው ፡ የሚከፈለውን ፡ ጠቅላላ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ዝቅ ፡ ለማድረግ ፡ ስለሆነ ፡ ሁኔታው ፡ ማቻቻልን ፡ የመሰለ ፡ ነው ። መሬት ፡ ለአውራ፡ ጐዳና ፡ ተብሎ ፡ ሲለቀቅ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ በሙሉ ፡ የሚወሰድበት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ተደጋጋሚ ፡ አይደለም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆነው ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ በቂ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ መሬትና ፡ በአውራ ፡ ጐዳናው ፡ ግራ ፡ እና ፡ ቀኝ በቂ ፡ የሆነ ፡ "የመተላለፊያ ፡ መብት" ብቻ ፡ ነው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ መሬት ፡ የተወሰደባቸው ፡ ባለንብረቶች ፡ ከድሮ ፡ መሬታቸው ፡ ቀሪ ፡ ስለሚኖራቸው ፡ አዲሱ ፡ ጐዳና ፡ በመሠራቱ ፡ በቀሪው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ እንደሚያስከትልላቸው ፡ አይጠረጠርም ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገጠር ፡ መሬት፡ዋጋ፡በቅጡ የተሰበሰበ ፡ ማስረጃ ፡ የለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በአብዛኛው ፡ ክፍል ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ አጠገብ ፡ የሚገኘው ፡ መሬት ፡ ዋጋ ፡ ከመንገድ ፡ ርቆ ፡ ከሚገኘው ፡ መሬት ፡ ዋጋ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ እጥፍ ፡ ይሆናል ። አውራ ፡ ጐዳናው፡ከመሠራቱ ፡ በፊት፡የነበረው ፡ ያንድ ፡ መሬት ፡ ዋጋ ፡ እና ፡ አውራ ፡ ጐዳናው ፡ ከተሠራ ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ ያካባቢው ፡ የመሬት ፡ የዋጋ ፡ ልዩነት ፡ ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሬት ፡ ሲያስለቅቅ ፡ መክፈል ፡ የነበረበትን ፡ የኪሣራ ግምት ፡ ከዚህ ፡ የመሬት ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ ጋራ ፡ ለማቻቻል ፡ ይችላል ።

## መደምደሚያ ።

ለመደምደሚያ ፡ ያህል ፡ የሚከተሉትን ፡ አሳቦች ፡ እናቀርባለን ፡— ምንም ፡ እንኳን ፡ ስለ ፡ መሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ የሚደነገጉት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጾች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ አይቃረኑም ፡ ብንል ፡ ለአ

24. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፩ሺ፬፻፸፩ ፡ (፩) ።

25. እንደ ፡ አጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፬ ፡ (፪) . የእንግሊዘኛው ፡ ቅጂ ፡ ከመጀመሪያው ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቅጂ ፡ በትክክል ፡ የተተረጐመ ፡ አይደለም ። የፈረንሳይኛው ፡ ቅጂ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ኰሚቴ ፡"tent Compte . . . de la plus - volue Procurée Par les trauaux Publics au *Surplus* de la Propriété" (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ይላል ። የዚሁ ፡ ቍጥር ፡ የአማርኛ፡ ቅጂ ፡ የፈረንሣይኛው ፡ ቅጂ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ ነው ።

26. ይህም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በመጀመሪያው ፡ የሥራ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ መሬቱን ፡ ቢያስለቅቅ እንደሚጠቅመው ፡ ያሳያል ። ይኸውም ፡ የቀሪው ፡ መሬት ፡ ዋጋ ፡ ስለጨመረ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ሥራውን ፡ የሚያሠራበትን ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሠፈር ፡ የመመስረቻ ፡ ቦታና ፡ ለወደፊቱ ፡ የጥገና ፡ ሥራም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ደንጊያ ፡ በቀላሉ ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሬት ፡ የማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ ከሚሰጠው ፡ የአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ በቀር ፡ አዋጁ ፡ በሙሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ ተሽሯል ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንም ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ እንዲፈጽም ፡ ይገደዳል ፤ በቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፭ ፡ (፪) የሚገኘው ፡ የማቻቻል ፡ አሳብ ፡ በደንብ ፡ ከተሠራበት ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፡ ብለን ፡ ብንገምትም ፡ ሁኔታው ፡ በጣም ፡ አስጊ ፡ አይሆንም ። ለቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፭ ፡ (፪) ፡ መደንገግና ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ከሚሰጥበት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ የመሬት ፡ አለመገኘት ፡ የተሰጠው ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ መንግሥት ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ብሎ ፡ በሚፈጽመው ፡ ሥራ ፡ የግል ፡ ባለ ፡ ንብረቶች ፡ በጣም ፡ ሲጠቀሙ ፡ የነዚህ ፡ ባለንብረቶች ፡ ኪሣራ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከሚያገኙት ፡ ቀጥተኛ ፡ ጥቅም ፡ ካልበለጠ ፡ በቀር ፡ መንግሥት ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ሊከፍላቸው ፡ አይገባም ፡ የሚል ፡ ነው ። የአውራ ፡ ጐዳና፡ ባለሥልጣንን ፡ ባቋቋመው ፡ አዋጅ ፡ መፍትሔና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፭ ፡ (፪) ፡ መፍትሔ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ ተፈጻሚ ፡ በሚሆንበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡— አንቀጽ ፡ ፩ሺ፬፻፸፭ ፡ (፪) ፡ እያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ለብቻው ፡ የሚያቀርበውን ፡ ችግር ፡ ለመመርመር ፡ ሲያስችል ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ግን ፡ የተድበሰበሰ ፡ አመራመርን ፡ የያዘ ፡ ነው ። ለመሬት ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ አይከፈልም ፣ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ለሚገኙት ፡ ነገሮች ፡ ግን ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ይከፈላል ።

አንቀጽ ፡ ፩ሺ፬፻፸፭ ፡ (፪) ፡ በያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ሚዛናዊ ፡ አመራመር ፡ እንዲደረግ ፡ ከመፍቀዱም ፡ ሌላ ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ቀጥተኛ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንን ፡ ባቋቋመው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ከመሬት ፡ ሌላ ፡ ለተወሰደው ፡ ንብረት ፡ በመሠረቱ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈል ፡ ግዴታ ፡ ሲኖር ፡ በቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፭ ፡ (፪) ፡ መሠረት ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዲቻቻል ፡ የሚደረግበት ፡ መንገድ ፡ አለ ።[27] ለዚህም ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆነው ፡ ለቡና ፡ ዛፍ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ አከፋፈል ፡ ችግር ፡ (ፕሮብሌም ፡) ነው ። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንን ፡ ባቋቋመው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የቡና ፡ ዛፎች ፡ "አዝመራዎች ፡ አትክልቶችና ፡ ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡" ስለሆኑ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ይከፈልባቸዋል ።[28] ብዙ ፡ የቡና ፡ ዛፎች ፡ በአሉበት ፡ እና ፡ የዛፎቹን ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ በገበያ ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ መክፈል ፡ ከፍተኛ ፡ ወጪን ፡ በሚጠይቁ ፡

27. የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ አዋጅ ፡ የመጀመሪያው ፡ "የጥቅም ፡ ሚዛን" የሚለው ፡ በሰብሎችና ፡ በቤቶች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ሲሆን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ተፈጻሚ ፡ አለመሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ። በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ንብረቶችን ፡ የማስለቀቅ ፡ ተግባር ፡ የሚያከናውኑ ፡ ሕዝቡ ፡ መሬቱ ፡ በከፊል ፡ ያለግምት ፡ ከሚወሰድበት ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ ቤቱ ፡ ተፈላጊው ፡ ግምት ፡ በፍጥነት ፡ ሳይሰጠው ፡ ሲወሰድበት ፡ የሚቃወም ፡ መሆኑን ፡ አስረድተዋል ። "የጥቅም ፡ ሚዛን" ወይም ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፭ ፡ (፪) ትክክለኛ ፡ ሲሆኑ ፡ የሚችሉት ፡ ጠቅላላ ፡ ዋጋቸው ፡ ከቍጥር ፡ በሚገባበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ቀሪው ፡ ንብረት ፡ ያገኘው ፡ የዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ በጽሑፉ ፡ የሰፈረ ፡ ቢሆንም ፡ መሬቱ ፡ በሚወሰድበት ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ ጭማሪ ፡ መገንዘብ ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። ከቀሪው ፡ ንብረት ፡ የዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ ጋር ፡ የሚቻቻለውን ፡ ኪሳራ ፡ ግን ፡ ወዲያውኑ በግልጽ ፡ ለመገንዘብ ፡ ይችላል ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ በመሠራቱ ፡ ቤቱ ፡ የፈረሰበት ፡ ሰው ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ ይፈልጋል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ ለመሥራትም ፡ ሆነ ፡ ለመግዛት ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ። ከቀሪው ፡ መሬት ፡ በከፊል ፡ ካልሸጠ ፡ በቀር ፡ በአውራ ፡ ጐዳናው ፡ መሠራት ፡ ምክንያት ፡ ቀሪ ፡ መሬቱ ፡ በጨመረው ፡ ዋጋ ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ።

28. አንቀጽ ፡ ፳ ፡ (መ) የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥጥር ፡ ፩፻፲፭ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳ ።

ቦታዎች ፡ የመሬቱ ፡ ባለንብረቶች ፡ ለቡና ፡ ዛፎች ፡ የሚደርሳቸውን ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንፈልግም ፡ ካላሉ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ አዲሱን ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ አይሠራም ፡ የተባለበት ፡ ጊዜ ፡ መኖሩ ፡ ይነገራል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ መንገድ ፡ አግኝተው ፡ ለቡና ፡ ዛፎቻቸው ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ያለማግኘትና ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የቡና ፡ ዛፎቻቸው ፡ እያሉ ፡ መንገድ ፡ ያለማግኘት ፡ ምርጫ ፡ ቢኖራቸውም ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ አስገዳጅ ፡ እርምጃ ፡ ማለት ፡ በሕግ ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ እንዲያጡ ፡ ማድረጉ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ። ከሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ በተለይ ፡ በአውራጃ ፡ ገዢዎች ፡ አማካይነት ፡ የሚመጣው ፡ ማስገደድ ፡ ምርጫው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ የተደረገ ፡ አለመሆኑን ፡ ያስረዳል ።[29] ቊ ፡ ፩ሺ፱፻፷፰ ፡ (፪) ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ሊሠራ ፡ ስለሚችልና ፡ እጅግ ፡ ሚዛናዊ ፡ የሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥበት ፡ ስለሚቻል ፡ ጥቅሙ ፡ ጉልህ ፡ ነው ። ባንድ ፡ ክፍል ፡ ለሚገኙ ፡ አብዛኞች ፡ ባለ ፡ ንብረቶች ፡ ባልተወሰደው ፡ መሬት ፡ የሚገኘው ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ ከጠፉት ፡ የቡና ፡ ዛፎች ፡ ኪሣራ ፡ ግምት ፡ ሊበልጥ ፡ ሲችል ፡ ለሌሎች ፡ ባለ ፡ ንብረቶች ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ የተጐዱት ፡ ባለ ፡ ንብረቶች ፡ ጠቅላላውን ፡ የዋጋ ፡ ኪሣራ ፡ የሚመጣጠን ፡ በቂ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ሊከፈላቸው ፡ ይገባል ።[30]

በመጨረሻም ፡ ለጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ለመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ ቢጠቀምበት ፡ የተሻለ ፡ ነው ። አንዱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ዓላማ ፡ በተለያዩት ፡ የሕግ ፡ ክፍሎች ፡ መካከል ፡ የማስለቀቅም ፡ ሕግ ፡ ጭምር ፡ አንድነትን ፡ ለመፍጠር ፡ ነው ።[31] የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የራሱን ፡ የማስለቀቅ ፡ ሕግ ፡ ካገኘ ፡ እና ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ አይቃረንም ፡ ከተባለለት ፡ መሬት ፡ የሚያስለቅቁ ፡ ሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶችም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንን ፡ አርአያ ፡ ሳይከተሉ ፡ አይቀሩም ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ለዚህ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚና ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ፡ የአሁኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጐች ፡ አንዱ ፡ ለሆነው ፡ ለመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሕግ ፡ መጥፎ ፡ አጋጣሚ ፡ ይሆናል ።

---

29. ደራሲው ፡ የአንድ ፡ ቀበሌ ፡ ሕዝብ ፡ የአውራ ፡ ጐዳናን ፡ ሥራ ፡ የሚቃወም ፡ ምርጫ ፡ ያደረገበት ፡ ጊዜ መኖሩን ፡ አልሰማም ።

30. የ"ጥቅም ፡ ሚዛን" ዋና ፡ ችግሩ ፡ ምንም ፡ ጉዳት ፡ ሳይደርስባቸው ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ የሚያገኙትን ፡ ሰዎች ፡ ከቊጥር ፡ አለማስገባቱ ፡ ነው ። ለዚህም ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑት ፡ ለሕዝብ ፡ ተፈላጊ ፡ በመሆን ፡ መሬት ፡ ሳይወሰድባቸው ፡ በአዲሱ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ መሠራት ፡ የመሬታቸው ፡ ዋጋ ፡ የሚጨምር ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። በመንገዱ ፡ መሠራት ፡ ምክንያት ፡ መሬታቸውን ፡ የሚያጡ ፡ ባለመሬቶች ፡ ለመንገዱ ፡ መሠራት ፡ ከሚደርሳቸው ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ የሚከፍሉ ፡ ከሆነ ፡ ትክክለኛ ፡ ሚዛን ፡ ለመፍጠር ፡ መሬታቸው ፡ ያልተወሰደባቸውንም ፡ ሰዎች ፡ የመሬታቸው ፡ ዋጋ ፡ ስለሚጨምር ፡ በዚያው ፡ መሠረት ፡ ማስከፈል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ "የማቻቻያ" ክፍያ ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

31. ለሕዝብ ፡ ተፈላጊ ፡ ሆነው ፡ ለሚወሰዱ ፡ ንብረቶች ፡ ግምት ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላላው ፡ ትክክለኛና ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ግምት ፡ ለመስጠት ፡ እንዲቻል ፡ ለሕዝብ ፡ ተፈላጊ ፡ ሆነው ፡ የሚወሰዱ ፡ ንብረቶችን ፡ ለማንኛውም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚመርጥና ፡ የሚገምት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ በአገር ፡ ግዛት ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ማቋቋም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ ተሰንዝሯል ። ይህንን ፡ ሥራ ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ወስኖ ፡ ማሠራቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ትክክለኛነትንና ፡ በሥራው ፡ ልዩ ፡ እውቀት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ለማስገኘት ፡ ይችል ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለሕዝብ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ንብረቶችን ፡ በግምት ፡ በመውሰድ ፡ ሥራቸውን ፡ የሚያከናውኑ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ የሥራ ፡ ቅልጥፍናን ፡ የሚቀንስ ፡ ሁኔታ ፡ (ቢዩሮክራሲ) ፡ ያስከትላል ፡ ብለው ፡ ሊቃወሙ ፡ ይችላሉ ። ለመንግሥት፡ ፕሮዤዎች ፡ መሬት ፡ የማግኘቱ ፡ ተግባር ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ የሚወሰን ፡ ከሆነ ፡ ሥራውን ፡ ከአገር፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይልቅ ፡ የመሬት ፡ አያያዝና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ ቢወስደው ፡ የተሻለ ፡ ይሆናል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይልቅ ፡ በመሬት ፡ ጉዳይ ፡ አዋቂዎችን ፡ በማሰልጠን ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የመሬት ፡ አያያዝና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ።